# ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ቀንድ የአካባቢ ማዕከልና ኔትዎርክ በማዕከሉ ውስጥ ለሚገኘው ካፌ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ሁለት የሥራ መደቦች ብቁ አመልካቾችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል።

1. የሥራ መደቡ መጠሪያ : የምግብ ዝግጅት ዋና ሃላፊ /ዋና ሼፍ/

ፆታ : ወንድ ወይም ሴት
ብዛት : አንድ
የቅጥር ሁኔታ : በኮንትራት
የሥራው ዓይነት

1. የመ/ቤቱን የዕለት ከዕለት የምግብ ሥራ እና ሻይ ቡና በሃላፊነት ማዘጋጀት
2. በሠራተኛው ፍላጎት መሰረት ዕለታዊ ሜኑ ማውጣት
3. ለዕለታዊ ሜኑ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ዝርዝር ማዘጋጀት
4. ለሥራው አስፈላጊውን በጀት ማዘጋጀት
5. አላቂ የምግብ እና መጠጥ ዕቃዎችን በመከታተል ግዢ መፈፀም
6. የቁርስ፣ የምሳም ሆነ የሻይ/ቡና አገልግሎት ለሠራተኛው በሰዓቱ እንዲደርስ ማድረግ
7. የመገልገያ ዕቃዎችን እና የማዕድ ቤቱን ንፅህና በአግባቡ መጠበቅ
8. ሌሎች ተዛማች የምግብና ሻይ/ቡና ሥራዎችን እንዳስፈላጊነቱ ማከናወን
9. መጠነኛ የኮምፒውተር ዕውቀት ቢኖረው ይመረጣል።

ተፈላጊ የትምህርት ችሎታ : እውቅና ካለው የሆቴል ማሰልጠኛ ተቋም በምግብ ዝግጅት ዲፕሎማ ያላት/ያለው

የሥራ ልምድ : በምግብ ዝግጅት ስራ አምስት ዓመት

2. የሥራ መደቡ መጠሪያ : ረዳት የምግብ አዘጋጅ /ረዳት ሼፍ/

ፆታ : ሴት
ብዛት : አንድ
የቅጥር ሁኔታ : በኮንትራት
የሥራው ዓይነት

1. የመ/ቤቱን የዕለት ከዕለት የምግብ ሥራ በአግባቡ ለማዘጋጀት ለዋናው የምግብ ቤት ሃላፊ አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ ማድረግ
2. ለዕለታዊ ሜኑ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ዝርዝር በማዘጋጀት ለዋናው ምግብ አዘጋጅ ለአስተያየት ማቅረብ
3. ለዕለቱ የሚስፈልገውን እንጀራ መጋገር

4. የቁርስ፣ ምሳ እና የሻይ/ቡና አገልግሎት ለሠራተኛው በሰዓቱ እንዲደርስ አብሮ መስራትና እገዛ ማድረግ
5. የሸያጭ ኩፖን በመሰብሰብ ለኮሚቴው የሂሳብ ሃላፊዎች ማስረከብ
6. የማዕድ ቤቱን ጠቅላላ የወጥቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ አልባሳት እና የክፍሉን ንፅህና በአግባቡ መጠበቅ
7. ከማዕድ ቤቱ የሚወጣውን ተረፈ ምርት/ቆሻሻ በጊዜው ማስወገድ
8. ሌሎች ተዛማጅ የምግብና ሻይ/ቡና ሥራዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማከናወን

ተፈላጊ የትምህርት ችሎታ : እውቅና ካለው የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በደረጃ 2፣ ደረጃ 3 ወይም በደረጃ 4 በምግብ ዝግጅት የሰለጠነ/ችና ሰርትፊኬት ያላት

የሥራ ልምድ : እንደ ትምህርት ደረጃው ቅደም ተከተል በምግብ ዝግጅት ሥራ የአምስት፣ የአራት እና የሦስት ዓመት የሥራ ልምድ

ለሁለቱም ክፍት የሥራ ቦታዎች  የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ችሎታዎች

- ከሠራተኛው ጋር ተግባብቶ መሥራት
- የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማርካት ጥረት ማድረግ
- የሥራ ሰዓት ማክበር
- የሥራ ጫናን መቋቋም

ለሁለቱም የስራ መደቦች

ደሞዝ፡ በድርጅቱ ስኬል መሰረት

ጥቅማጥቅም : የስልክ አበል፣ የቤት ኪራይ አበል እና ጧትና ማታ ሰርቪስ ያመቻቻል፡፡

የሥራ ቦታ : የአፍሪካ ቀንድ የአካባቢ ማዕከልና ኔትዎርክ ዋና መ/ቤት - ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ግቢ ውስጥ

የምዝገባ የመጨረሻ ቀን : ሚያዚያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም.

አመልካቾች በጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል ግቢ ውስጥ በሚገኘው የአፍሪካ ቀንድ የአካባቢ ማዕከልና ኔትዎርክ ዋና መ/ቤት ወይም አራት ኪሎ በሚገኘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኮምፒውቴሽናል እና የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ሕንፃ ዘጠነኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 903 በመገኘት፤ እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ አሜይል (recruitment@hoarec.org) የትምህርት፣ የስልጠናና የስራ ልምድ ማስረጃዎችን አያይዘው ከማመልከቻ ጋር ማስገባት ይችላሉ፡፡